# Citizens Charter

## for a Democratic Ethiopia

*A Common Cause for Freedom, Prosperity, and National Renaissance*



# የዜጎች ቃልኪዳን

## ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ

# የዜጎች ቃልኪዳን ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ

## የጋርዮሽ ንቅናቄ ለዴሞክራሲ፥ ለብልጽግናና፥ ለብሄራዊ ተሓድሶ

### ክፍል ፩ -- መግቢያ

**ይህ የዜግነት ቻርተር** (ቃል-ኪዳን፤ ሕገ-መሠረት) ከፖለቲካዊ ቡድናዊነት ነጻ የሆነ፤ የድህረ ሶሻሊስትና የድህረ ዘረኛነት፣ ባጭሩ ሁሉን-አቀፍ የሆነችዉን አዲሲቷን ኢትዮጵያን የሚቀርፁ ምሰሶዋዊ መርሆዎችን ያካተተ የሲቪክ ንቅናቄ መመሪያ ሰነድ ነዉ። ኢትዮጵያ ከየት ወደ የት ለሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ የማያዳፍር መልስን ያቀፈ ራእይን የሚያስተጋባ የኩሩ ዜጎች ሰንደቅ ዓላማ ነው። ይህም ማለት፡-

- ቃልኪዳኑ ግልጽና ሁሉን-አቀፍ ሕብረተሰብ ለመገንባት የሚጠቅሙ የሲቪክ ባህሎችን ለማዳበር፤
- በዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት፤ሉዓላዊነት፣ ማህረሰባዊ ራስ-በራስ መስተዳደርን የመሳሰሉ ልምዶች እንዲሰፍኑ በጠቅላላው መልካም የስልጣን አጠቃቀም ስነ-ምግባርን እውን ለማድረግ ለተነሳሱ ዜጎች፣ የሲቪክ ማህበራትና የፖለቲካ ፓርቲዎች የአንድነትና የዎል ራአይና መመሪያ ሆኖ እንዲያገለግል፤
- በዓለም-አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ የሰብእዊ፣የሲቪል፣የባህልና የፖለቲካ ሁለንተናዊ መብቶች በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በነግ-በኔ ስሜት በዜጎችም እንዲጠበቁ የሚያስችል የሲቪክና የፖለቲካ ጥምር አንቅስቃሴን እውን ለማድረግ በልበ-ንጹህነትና በንቃተ-ህሊና መመራት አስፈላጊነቱን ለማስገንዘብ፣
- የረጅም ጉዞ አንቅስቃሴውን ፍሬያማ ለማድረግ ደግሞ ለግለሰብ አርነትና ክብር መጠንቀቅ፣ የህብረተሰብን ጥቅም ማቀፍ፣ የተለያዩ ባህሎችን ማክበርንና አዎንታዊ አመለካከት መኖርን የመሳሰሉ መሠረታዊ እሴቶችን መደገፍ ዋና ተግባር ነው። ስለሆነም የዛሬው ትውልድ የነገይቱን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚገነባባቸው የኢትዮጵያዊነት መንፈስና የስልጣኔያችን መለዮች መሆናቸውን አጉልቶ ለማሳየት፣
- አበው ድር ቢያብር አንበሳ ያስር አንዳሉት፤ የሲቪክ ማህበራትን ንቃትና በአንድ ግንባር ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የምንሻው ህዝባችንን ከቀማኛ የፖለቲካ ነጋዴዎችና ከጨቋኝ መንግስታዊ ስርዓት ለማውጣት ብቻ ሳይሆን ተመልሶም ከጭቆና እሳት እንዳይማገድ የህዝብ ወኪሎች ዘብ መቆም ዋስትናዊ ሚና ስላለው ነው። ይህም በመሆኑ መብትና ግዴታዎችን በጽኑ እውን ለማድረግ የሚካሄደውን ትግል ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንዲደገፉ ጥሪውን ለማስተጋባት፣ በመጨረሻም
- ኢትዮጵያውያን "የገዥና የተገዥ" ባሕልን ለዘለቄታው አውልቀው ጥለው በነጻ መብትና ግዴታ ጥምሮች ላይ የተመሰረተ አዲስ የአስተዳደር ባህል እንዲያቅፉ እምቢልታውን ያስተጋባል። ከእንግዲህ ወዲያ የምንዘረጋው ሥርዓት ሃቀኛነትንና ዜጎችን ሉዓላዊ ያደረገ፣ የምንመርጣቸዉ

መሪዎችም ለሕዝብ አገልግሎትና ተጠያቂነት የገቡትን ቃል በመወጣትና ባላመወጣት የሚመዘኑ እንዲሆን ስልምንመኝ ነው።

ይህ ቃል-ኪዳን፣ እገሌ ከእገሌ፣ትንሽ ትልቅ ሳይባል ኢትዮጵያውያን ሁሉ ጠንካራ የጋራ እንቅስቃሴ አድርገው ለእኩልነትና ለፍትህ የቆመ መንግስት በመመስረት ዜጋዊ ነጻነትን እንዲያስከብሩ የተዘጋጀ ሕገ-መሠረት ነው። የሕዝብ ተጠሪ ነን ለሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት ሁሉ ይህንን ሕገ-መሠረት እንዲቀበሉና እሰነዱ ውስጥ የተዘረዘሩትን መርሆዎችና አላማዎች በድርጅታዊ ፕሮግራሞቻቸው ውስጥ እንዲያካትቱ አጥብቀን የምንጠይቀው ከዚህ ከኢትዮጵያዊነት መንፈስ በመነሳት ነው።

> ከእንግዲህ ወዲያ የምንዘረጋው ሥርዓት ሃቀኛነትንና ዜጎችን ሉዓላዊ ያደረገ፣ የምንመርጣቸዉ መሪዎችም ለሕዝብ አገልግሎትና ተጠያቂነት የገቡትን ቃል በመወጣትና ባላመወጣት የሚመዝን መሆን

## ክፍል ፪ -- ኢትዮጵያ ከየት ወደ የት?

እያንዳንዱ ትውልድ ካባቶችና ከናቶች የተወረሰውን አሻሽሎ የማቅረብና ኢትዮጵያን የማስከበር ኅላፊነት ተሸካሚ ነው። የአሁኑ ትውልድ ብሄራዊ ማንነቱን መተርጎምና ማስረገጥ ዓብይ ተግባሩ ነው። ዘመናዊዋ ኢትዮጵያም ሁሉም ዜጎቿ ገጽታቸውና ተምሳሌታቸው በሃገር-አቀፍ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ይዘቶች የሚያንጸባርቁባት አገር መሆንም እንዳለባት አያከራክርም።

እንደሚታወቀው ቀደምት የኢትዮጵያ ታሪክን አብዛኛ ይዘቶች በጥራዝ-ነጠቅ ትንታኔ ተደናግረው ባደናገሩ፣አልፎም ቅንነትና በቂ እውቀት በጎደላቸው ወይንም በጠባብ ጥቅም በታወሩ ምሁራንና በተገንጣይ ንቅናቄዎች ሲዛባ ቆይቷል። ስለሆነም፣ የአሁኑን ትውልድ ምኞትና ተስፋ አዎንታዊ ለማድረግና ሀገሪቱ በአሁኑ ወቅት የገጠማትን አስቸጋሪ ሁኔታ በመገንዘብ፣ በአመለካከት አንፃር የጋራ ስምምነት እንዲኖርና ታሪካችንን በውል ተረድቶ የወደፊት ምኞታችንን መንደፍ አንገብጋቢ ተግባራችን ነው። የኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት በቀላሉ የማይካዱ የውርስ ገጽታዎች ስላሉት ለተነሳንበት ዓላማ የሚጠቅሙትን ለምሳሌ ያህል እንጠቁማቸው፡-

- ባለፉት ብዙ ምዕተ-ዓመታት አንዴ ሲጠብ አንዴ ደግሞ ሲሰፋ በኖረው የኢትዮጵያ ግዛት ጎልተው የሚታወቁ በአንድ ጎሳ/ነገድ ስም ብቻ ወይንም ክልላዊነት የተመሰረቱ ሉዓላዊ መንግስታት አልነበሩም። እርግጥ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪዎች ወይንም የሃይማኖት ተከታዮች በጉልበት አንዱ ሌላውን አስገብሮ ለመብላት ቢጥርም፣ አብዛኛውን ጊዜ ተዛምዶና በባህል ተወራርሶ ኖሯል። ይህ ዘር-አልባ

> በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በአንድ ዘር ስም ብቻ የገዙ ንጉሶች ወይንም በክልል-ገደብ የተቋቋሙ “ሉዓላዊ” መንግስታት አናቅም።

የሆነ ባህል እርስ-በርስ መዋረሩ ተወግዶ የሚቀረዉ ፍሬ ባህል ዘመናዊ ዲሞክራሲን ለመገንባት ምቹ መንደርደሪያ መሆኑ አያከራክርም፤

- በሀገሪቱ ውስጥ ክርስትና፣እስልምናና ባህላዊ የሃማኖት ሥርዓቶች ከመቻቻል አልፈው በመተቃቀፍ መኖራቸው የአንጋፋዋ ኢትዮጵያን አብነት ያስመዘግባል። ሰማኒያ ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ኢትዮጵያ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሀገር በመሆኗ፣ ተባብረው የሚኖሩበትንና የአናሳዎቹን መብት ለማስከበር የሚያስችል ዲሞክራሲያዊ [ሕዝባዊ] ሥርዓት እንዲፈጠር ማድረግ አስፍላጊነቱ ግልጽ ነው፤

- አልፎ አልፎ ከታዩት ከባድ የፈተና ዘመኖች በስተቀር ኢትዮጵያውያን በታሪካቸው ጠንካራ መለያዎችን ተጋርተዋል። በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ልዩነትም ቢሆን ቆለኛው ከደገኛው፣ አርሶ-አደሩ ከአርቢ-አደሩና ከነጋዴው ጋር በኢኮኖሚ ተደጋጋፊነት፣ በፖለቲካ ተፎካካሪነትና በባህል ተወራራሽነትን አፍርተዋል። ገዳማት፣አድባራትና መስጊዶች እንዲሁም የማህበረሰብ ተቋማትና የሰፈር ሽማግሌዎች ተቃራኒ ፍላጎቶችን በማስታረቅ ረገድ ለወደፊት የሚበጁ ሰላማዊ አደራዳሪ ተቋሞችን የምንገነባበት የባህል ቅርስ አጎናጽፈውናል፤

> ኢትዮጵያ በታሪኳ ሌሎችን የሚያስቀና በሕዝቦቿ መካከል ከመቻቻል አልፎ ወደመተቃቀፍ የደረሰ ግንኙነት የሰፈነባት አገር

- ኢትዮጵያ በአፈ-ታረክ (ቃላዊ) ብቻ ሳይሆን የረጅም ስልጣኔዋ መለዮ በሆነው ፅሁፈ-ታሪክን (ፊደላዊ) በመጠቀም ክትውልድ ወደ ትውልድ የሞራል፣ የፖለቲካና የቁሳቁስ ባህሎችዋን ስታስተላልፍ የኖረች አገር ናት። ከውጭ ስልጣኔዎች ጋር ባላት ግንኙነት ዓይነ-ጭፍን ኩረጃ ሳይሆን የሚበጇትን ተቀብላ በረቀቀ ዘዴ ከባህሏ ጋር አጣጥማ የማስፋፋት ችሎታ የነበራትም አገር ናት። ለምሳሌ የሃይማኖት ገጽታን በሚመለከት፣ ከሌሎች አገሮች የሚለያት አርማዋ ከአፍሪካ እሴቶቻችን ጋር የተጣመሩ የአይሁዳዊ፣ የክርስትናና የእስልምና እምነቶች አብረዉ ለብዙ ዘመናት በሰላም መኖራቸው ነው፤ እንዲሁም

- የዛሬዋ ኢትዮጵያ ከፍተኛ የጦርነትና የፖለቲካ ሽብሮችና ውጥንቅጦች ጠባሳዎች ይታዩባታል። ከነዚህም በኢጣሊያ ሁለት ጊዜ ይተፈጸመባት ወረራዎችና ከዚያ ማግስት የተማከለ መንግስታዊ ቢሮክራሲ ለመፍጠር የተካሄዱ ሹኩቻዎች፣ በ1966 ዓ.ም. በአብዮት ስም የወታደር ሶሻሊዝምን የተሞከረበት የመከራ ዘመን፣ በኤርትራ መዋሃድና እንደገና መገንጠል ወቅት የተካሄደው እርስ-በርስ ጦርነት፣ ኢትዮጵያዉያንን በአንድነት አርማ ያስተሳሰሩትን ብሄራዊ ተቋማት ለማፈራረስና የአገሪቱን ኢኮኖሚ፣መንግስታዊ ስልጣንና ሕብረተሰባዊ ሃረጎችን የዘረጋበትን ጎጠኛ ስርአትን መጥቀስ ይበቃል።

የነዚህ አስከፊ ጥቃቶች ውጤቶችና ፍልሚያዎች ብዙ ናቸው፡- የርስ-በርስ መተማመን መቦርቦር፤ በልጆቻችን አእምሮ በሃገር ከመኩራት ወደ ማፈር ቀስ በቀስ መለወጥ፣ የድህነት መናርና የወጣቱ ተስፋ ማጣት፣ ቡድናዊነትና ወገናዊነት ከልክ አልፈው ሆዳምነትና ግለኝነት የበግ ለምድ መልበስን መጥቀስ ይቻላል። ከደርግ ይባስ ተብሎ በሲቪል ሰርቪስና በጦር/በደህንነት ኃይል ቁልፍ ቦታዎች ላይ የፖለታካ ጀሌዎች ተሰግስገውበት ይገኛል።

የገዢ ፓርቲዎች ካድሬዎች ጠብና ግጭት ማስወገጅያ ባህላዊ ልምዶችን በማጥፋትና ሽማግሌዎችን በመወንጀል ሕዝቡ በስፈር ዓበውና በመንግስት ሹማምንት ላይ እምነትን አሳጥተውታል።

ይህ ስር እየሰደደ የመጣ ቅውሰት ጎላ ወዳሉ ሁለት ድምዳሜዎች ላይ ያደርሰናል። 1ኛ) የምንገነባው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በባለቤትነት እንድንቀበለውና እንድንኮራበት ከተፈለገ ጥራት ባላቸው የመንግስታዊ ስልጣን አያያዝ ባህሎቻችን ላይ የተመሰረተ መሆን እንደሚኖርበትና፤ 2ኛ) ለዘላቂ ብልጽግና፣ የዜጎችንም ሆነ የመንስትን ሉዓላዊነቶች ለማስክበርና ለአፍሪካ ቀንድ መሪነትን ለመጎናጸፍ ከውጭው ዓለም ጋር በጋራ ጥቅሞች ለይ የተመሰረተ ትስስር ሲዘረጋ መሆኑን ነው። የጋራ እድልን በጋራ ለመወሰን የሚያስችለንም ይህ ነው።

በአይበገሬነት የቆየውና ቢወድቅ ነጥሮ የሚነሳው ኢትዮጵያዊነት ስሜትና ጨዋነት ወደፊት ተራማጅ የመንግስት አወቃቀርና አሰራር የሰፈነበትን ስርዓት ለመዘርጋትና “የነፃ-ዜጋ” ልደትን ለማብሰር በር ከፍቶልናል። ነፃ ዜግነት የጋራ ጥቅምን ከግል ጥቅም ጋር አጣጥሞ የሚያራምድ የልበ-ሙሉ የኢትዮጵያዊነት አርማ ነው።

> “ነፃ ዜግነት” የጋራ ጥቅምን ከግል ጥቅም ጋር አጣጥሞ የሚያራምድ የልበ-ሙሉ ኢትዮጵያዊነት አርማ

የኢትዮጵያን ትንሳኤ በሚመለከት ይህ ሰነድ የሚያራምደውን ፅንሰ-ሃሳብ የሚያሳዩ ሦስት ዋና ዋና መሰረታዊ መርሆች ተቀምጠዋል። እነዚህም፣ 1) የሕዝብ ውክልናና አለኝታ ያለበት አስተዳደር፣ 2) ብዙሃኑ የአናሳዎችን መብት የሚያከብሩበት ባህላዊ ርዕይንት እና 3) የኢኮኖሚ ነፃነት ናቸው። እነዚህ መሰረታዊ መርሆዎች ተጨባጭ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ተሀድሶ ዕቅዶችን ለመንደፍ የሚያገለግሉ ምሰሶዎች ይሆናሉ። ሦስቱ የማይነጣጥሉ መሠረታዊ መርሆዎች ለዘላቂ ሰላም፣ጠንካራ ኢትዮጵያዊ ማንነትንና በፍትሓዊ መንገድ የህዝብ ባልስልጣንነትን ያንፀባርቃሉ።

## ክፍል ፫ -- የኢትዮጵያ መለዮ ዲሞክራሲ ምንድን ነው?

ዓርነት መስረታዊ ትርጉሙ ብዙ አማራጮችን ማግኘት ሲሆን፤ ለዲሞክራሲም ቅድመ መሰረቱ ነው። ዲሞክራሲ ደግሞ መሰረታዊ ትርጉሙ ነፃ ሕዝብ የመራጭ መብቱን በስራ ላይ የሚያውልበት የውሳኔ መስጫ መንገድ ነው። በህዝብ ሉዓልና የተመሰረቱ ወኪላዊ የዲሞክራሲ ይዘቶች--ግለሰባዊ (ሊበራል) እንዲሁም ወልአዊ (ሶሻል)--የዜጎችን መብቶችን (ማለት ህይዎትን፣ነጻነትን፣ሃብትን) በውክልና በማስከበር ደረጃ አብነትን የያዙ ናቸው። የዚህም መሰረቱ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙትን መብቶች ያካተተ ርዕሰ-ሕግ (Basic Law፤Constitution) በጽሁፍ መፅድቅ ነው። ለዚህም ነው ይህ የቃል-ኪዳን ስነድ መልካም የሆኑ ኢትዮጵያዊ እሴቶችንና ልንዘነጋቸው የማይቻለን የዘመናችን እውነታዎችን ያካተተ ርዕሰ-ሕግ እንዲዘጋጅ የሚጠይቀው።

ስለ አገራችን ዲሞክራሲ ያለን አመለካከት በአገሪቷና በሌሎች ተመሳሳይ አገሮች የፖለታካ ታሪክ ልምዶችና ተመክሮዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ የተጫኑብን ሶስቱ ህገ-መንግስቶች ይህ ነው የሚባል ፍትህ፣እኩልነትና ብልፅግና አለማስገኘታቸው ግልጽ ነው። በብልጣ-ብልጥ ገዢዎች እጅ የሕዝብ ማደናገሪያዎች ከመሆን አላለፉም። ነገር ግን በወረቀት ላይ የተቀመጡ ተገቢ መብቶች ይዋል ይደር እንጅ ሕዝቡ ሲነቃ እንዲከበሩለት ስለሚታገል ለዲሞክራሲያዊ ስርዓት ቀስ በቀስ ሥር መስደድ ቃሚነታቸውን መርሳት ስህተት ነው። ከአሸከራዊ አመለካከት ወደ ነፃ-ዜጋዊ አመለከካት በዚህ ወጣ-ገብ መንገድ ማለፍ የእድገት ዕጣ ነውና።

ከተመክሮ እንደተማርነው እንከን-የለሽ የወረቀት ርዕሰ ህግ በግብር ላይ መዋል የሚፋጠነው ትብብርንና የጋራ ኀላፊነትን ሳይታክቱ ለመብት ዘብ የመቆም ፈሊጥን ማዳበር ነው። በሰለጠኑት አገሮች ያንዱ መብት መገፈፍ የሁሉም መብት እንደመገፈፍ የሚቆጠረው አፍንጫ ሲመታ ዓይን ማልቀሱ አይቀርም እንድሚባለው ነው። ይኽ ባሕል በአገራችን ገና ጮርቃ ነው። ስለሆነም፣ ለጊዜው ምሽጋቸው በከተሞች የተወሰነው የፖለቲካ ድርጅቶች የገጠሩን መራጭ ማንቃትና መልሶም ከዚህ ሰፊ ሕዝብ ብልህ አስተሳሰብ መማር ግዴታቸው ነው።

ማንኛውም የመንግስት አስተዳደር መብቶችን ሲጥስ እያንዳንዱ ዜጋ ሕጋዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲችል በአለም-አቀፍ ደረጃ የሚሰራባቸው ስሌቶች በስነ-ስርዓት እንዲመዘገቡለት መጣር አለበት። ስለዚህ፣ ይህ ቃል-ኪዳን የሚደግፈው ርዕሰ ሕግ በሰብዓዊነታቸውና በዜግነታቸው ብቻ የሚገቧቸውን መብቶች ለጊዜው ስልጣን የያዘ አስተዳደር ሊጥሳቸው እንደማይችል በማያሻማ መንገድ የሚያስቀምጥ መሆን አለበት። ከብዙ በጥቂቱ እነዚህ መብቶች፦ ከበደልና ከፍርሃት ነጻ መሆንን፣የሕግ የበላይነት መስፈንን፣የማሰብና ሃሳብን በነፃነት መግለጽን፣ በአብይ የአገሪቱ ጉዳዮች ውሳኔ ላይ ተሳታፊ መሆንን፣ከችጋርና ድንቁርና ነጻ መሆንንና በሁሉም መስክ እኩል ዕድል ማግኘትን የሚያካትቱ ናቸው።

> **ይህ ስነድ የሚደግፈው ርዕሰ-ሕግ በሰብዓዊነታቸውና በዜግነታቸው ብቻ የሚገቧቸውን መብቶች መንግስት ሊጥሳቸው እንደማይችል በማያሻማ መንገድ**

ኢትዮጵያ ሊሚኖራት የሚገባትን ርዕሰ-ሕግ ሙሉ ይዘት በቅድሚያ ለመዘርዘር የዚህ ቃል-ኪዳን አላማም፣ ሃላፊነትም አይደሉም። ዳሩ ግን በውል ሊታሰብባቸው የሚገቡ አንዳንድ መሠረታዊ መመሪያዎችን ልንጠቅስ እንወዳለን። በዚህም መሰረት በዜጐችና በመንግሥት መካከል በግልጽ ውል ሆኖ የሚያገለግል ርዕስ-ሕግ፦

- በከፍተኛ የሕዝብ (በተለይም በወጣቱ ትውልድ) ውክልናና ተሳትፎ የሚዘጋጅ፣
- ለሁሉም ዜጐች የፖለቲካ እኩልነትን የሚያረጋግጥና፣
- የሴቶችን እኩል ባለስልጣናዊነት የሚያጐናጽፍ፣
- መሰረታዊ የኑሮ ፍላጎቶች ካልተሟሉ ሌሎች መብቶች ሁሉ ምንም ፋይዳ ስለማይኖራቸው የነዚህን መብቶች አውራነት የሚያረጋግጥ፣
- ዜጐች በመንግሥት ላይ ያላቸውን የመራጭ/አውራጅ በትረ-ሥልጣን በግልጽ የሚያስቀምጥ፣
- የሕግ በላይነትን የማክበር ባህል በሕዝብና በባለስልጣኖች ዘንድ ሙሉ በሙሉ እንዲሰርፅ የሚያመቻች፣
- የግለሰብ መብቶችን በማይጥስ መንገድ ሁሉንም ባህሎች ካለአድልዎ የሚያጠናክር፣
- ግልፅና አስተናጋጅ ማህበረሰብንና በውድድር ላይ የተመሠረተ የገባያ ኢኮኖሚ ስርዓትን የሚያጎለምስና፣ እንዲሁም
- የመንግሥት ሥራ አገልግሎትን በተመለከተ ግልፅነት፣ ታዛዥነትና ታማኝነት እንዲሰፍኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻች መሆን ይኖርበታል።

የምናምንባቸውን መርሆዎች በተግባር ልንተረጉማቸው ይገባል፤ ፋይዳ-ቢስ ወሬ ትርፉ ግብዝነት ነውና። ለዚህም ነው በአዲሱ የፖለቲካ ሥርዓት የህግ በላይነት እንዲሰፍን የግለሰቦችና የነፃ

ድርጅቶች ንቁ ጥበቃ የማያስፍልገው፤ አምባ ገነኖችም እነዚህን የመብት ሐዋርያዎች ምርኮኛ አድርገው፣ ምርጫንም የይስሙላ ለማካሄድ የሚዶልቱት። እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት አንድ ጉዳይ በአስከፊ ድህነት ላይ የሚኖር ሕዝብ መብቶቹን ለማስከበር ከእውቀት ይልቅ አቅም ስለሌለው ቁንጮ በሆነው በተማረው ክፍል አጋርነት ላይ መመካቱ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ርእሰ-መንግስትን በባለቤተኝነት የሚያቅፈው ዘላቂ ሰላምን፣ የህግ የበላይነትንና ፍትሕን አራማጅ ሆኖ ሲያገኘው ነው። ስለዚህ አዲሱ ርእሰ-ሕግ ሲረቅ ባለፉት ሀምሳ ዓመታት ከተደረጉት ጥረቶችና ልምዶች የተገኙ ትምህርችቶችን ያካተተና ከዚህ በታች በተዘዘሩት መሰረታዊ መመሪያዎች ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ቃል-ኪዳኑ ያምንበታል። ስለዚህ የዛሬው ትውልድ በባለቤትነት የሚጎናጸፈው መንግስታዊ ስርዓት የሚከተሉትን ይዘቶች ማንፀባርቅ ይገባዋል እንላለን፡-

**[ሀ] የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና ግዛት ማስከበር፡-**

የኢትዮጵያ ሕዝብ በረዥም ታሪኩ ነፃነቱንና አንድነቱን ጠብቆ በማቆየት በቀላሉ የማይበጠስ ዝምድናና ትስስር ፈጥሯል። ይህ የሕዝቡ ታረካዊ ቆራጥነትና መስዋአትነት መዘከር አለበት። ኢትዮጵያና ጐረቤቶቿም የቀጠና ውል በማጽደቅ ቋሚ ሰላምንና በጋርዮሽ ጥቅም መዛመድን ማጠናከር ይበጃቸዋል።

**[ለ] የግለሰብ መብቶች ቀደምትነት፡-**

ይህ ቃልኪዳን ኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊት ባትሆንም የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች እስር ቤት ሆና ቆይታለች የሚለዉን መሰረተ-ቢስ ቅጥፈትም ሆነ ከዚህ የሚፈልቀውን ከፋፋይ መፍትሄ አይቀበለውም። በሓቀኛ ዲሞክራሲ ስርዓት ይዘት እንደሚታወቀው የቡድን መብት የሚመነጨው ክግለሰብ መብት ስለሆነ ነፃ ግለሰቦች የሚኖሩባት አገር ጭቁን ቡድኖች ወይንም ወገኖች ሊገኙባት አይችሉም። "አንድ ዜጋ አንድ ድምፅ" ባለበት የአስተዳደር ሥርዓት፣ ግለሰቦች የፈለጉትን ድርጅት መደገፍ ከመቻላቸውም ሌላ ዘራዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ባህሎቻቸውን ማክበርና ማጎልመስ መብታቸው ነው። ይህም ሲባል ዴሞክራሲ የብዙሓን ፍላጎትን ብቻ የሚያስተናግድ ሳይሆን የአናሳ ቡድኖችንም መብት ካለገደብ የሚያስከብር ስርዓት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

> **የብዙ ቋንቋዎች ተናጋሪዎችና ኅይማኖቶች ተከከታዮች ባሉባት አገር "የግለሰብ መብቶችን" ከፍተኛ ቦታ የሚሰጥ ርዕሰ-ሕግ ለነፃነትናለዴሞክራሴያዊ ስርዓት ምሰሶ ነው።**

**[ሐ] ለሕልውና መሰረታዊ ፍላጎቶችን የማግኘት ዋስትና፡-**

በቂ ምግብ ማግኘት የህልውና መሰረት ስለሆነ ከፈጣሪ የተሰጠ ዓንጋፋ መብት ሆኖ በዘመናችን ይታያል። ስለዚህ ራሱን የሚያከብር መንግስት (ምንም ደሃ ቢሆን) በብዙ የሚቆጠሩ ዜጎቹ በረሓብ አያለቁ፤ ህጻናት በምግብ አጥረትና አለመመዛዘን አድገታቸው ሲኮላሸፍና በቀላሉ ሊወገዱ በሚችሉ በሽታዎች ሲለከፉ ቆሞ ሊያይ አይችልም፤ አይገባውም።

**(መ) ቢያንስ አንድ የብሔራዝዊ የስራ ቋንቋ አስፈላጊነት፡-**

ኢትዮጵያዊነት የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቃልኪዳን ናት። የዚችም የጋርዮሽ መለዮ አንዱ ገጽታ ሁሉም ዘመናዊ ዜጎቿ ቢያንስ ቢያንስ አንድ ብሔራዊ፤ አንድ ክፍለ-አገራዊና፤ አንድ አለም-አቀፋዊ ቋንቋ መናገር መቻላቸው ነው። አንድ የጋርዮሽ ብሔራዊ የስራ ቋንቋ በአገር ደረጃና በሁሉም አካባቢዎች የመደንገጉን ኣስፈላጊነት ለምሳሌ ብንጠቅስ አንደ ትምህርትና ፍርድ ቤት የመሰሉ መንግስታዊ አገልግሎቶች ለሁሉም ዜጋ ካለአድልዎ በቀላሉ መሰጠት ስለሚኖርባቸው ነው። ስለዚህ አገሪቱ አሁን ያላትን አቅም በመገንዘብ ለግዜው በአማርኛ

እንዲጀመር እናሳስባለን። ኦሮሚፋና የአለም ቋንቋ የሆነው እንግሊዝኛም ወደዚህ አውቅና ለመድረስ እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ ቃል-ኪዳኑ ይጠይቃል። ሌሎቹም ቋንቋዎቻችን በእንክብካቤ እንዲበለጽጉ እንደግፋለን።

### (ሰ) በብሔር ወይንም በጎሳ ያልተማከለ ርዕሰ-መንግስታዊ ስርዓት፡-

የሕዝባችንን የኑሮ ደረጃና ለሁለት ትውልድ ያህል የተዘረጉበት መንግስታዊ ስርዓቶች ካስከተሉት ችግሮች በመነሳት፣ የአስተዳደር አካላትን እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ በመዘርጋት ራስ-ገዝነትን ማስፋፋት አስፈላጊነቱ ግልፅ እየሆነ መጥቷል። የክፍለ ሃገር አስተዳሮች የድንበር ወሰኖች በታሪካዊ፣ ብሔረሰባዊ፣ በመልከዐ-ምድራዊና በኢኮኖሚያዊ ትስስሮች የተመሰረተ ሆኖ መነደፍ ይኖርበታል። እነዚህ ምን ሉዓላዊነት ሊኖራቸው የማይገባ የውስ ሃገር መስተዳሮችም ከአድገት አንጻር ተገቢ የሰዉና ድርጅታዊ ችሎታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

### [ረ] ሁሉን-ወካይ የፍትህ፡ የወታደርና የሲቭል አገልግሎቶች፡-

መሰረታዊ መብቶች ሊጠበቁ የሚችሉት የሀገሪቱን የዘር፣የብሔር፣የሃይማኖትና የጾታን ስብጥር የሚያንጸባርቁና በችሎታቸው የሚመረጡ የወታደር፣ የሲቪልና የደህንነት አገልግሎቶች ሲቋቋሙ ነው። እነሱም ሁለት መመሪያዎችን ማክበር አለባቸው፡- 1ኛ) የሲቭል አስተዳደሩ በወታደራዊና ጸጥታ ታቋማት አዛዥነቱን፣ 2ኛ) ሁሉም መንግስታዊ ተቋማት በመካከላቸውም ሆነ ከዜጎች ጋር ቅራኔዎች ሲፈጠሩ በህግ ፊት እኩልነታቸውን በመጠበቅ ወደ ነጻው የፍትህ ክፍል መሄድ እናዳለባቸው ነው።

### [ሸ] ነፃና ውድድራዊ የገባያ ስርዓት፡-

ማንኛውም ዜጋ የግል ንብረቱ ሕጋዊ ዋስትና አግኝቶ በፈለገበት የአገሪቱ ክፍል የመኖር፣ የመስራትና የማምረት መብት አለው። የግል ባለ-ሃብትም በነጻ ገበያ ተወዳድሮ የማትረፍ መብትም/ግዴታም አለበት። ውድድራዊ የገባያ ስርዓትን ለመገንባት መንግስት ከሚፈጽማቸው ሃላፊነቶች መካከል ዋነኞቹ፡- አድልዎ የሌለበት የውድድር ሥርአት መፍጠር፣ ዋጋን ማረጋጋት፣ ለሙስናና ለምርት ዝቅተኝነት የሚያመቹ መንግስታዊና የገዢ ፓርቲ ትርፍ-ፈላጊ ኩባንያዎችን መሸጥ ወይም መዝጋትና ለአቅመ-ቢስ ዜጎች የማሕበራዊ ደህንነትን ድጋፍ ማዘጋጀት ናቸው። በጠቅላላው የቀምቶ-በላ ስርዓት ተገርስሦ "ባለቤትነት ላምራቹ" በሚል የሰርቶ-በል ስሪት መተካት አለበት።

> ገዢም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ ጥቅሙን ለማራመድ ብሎ ድርጅታዊ የጦር ሃይል ወይንም ትርፍ-ፈላጊ ኩባንያዎች አቋቁሞ የዲሞክራሲና የገባያ ስርአቶቹን ስር በሰደደ

### [ቀ] ነፃና ተጠያቂ የሲቪክ ማህበራትና የፖለቲካ ፓርቲዎች፡-

በታዳጊ ዲሞክራሲዎች፣ በተለይም ደካሞቹ ዜጎችን በአጋርነት የሚያገለግሉ በርካታ የሙያ፣ የርዳታ፣ የምሁራንና የጋዜጠኞችና የሲቪክ ድርጅቶች በተለይ ጉልበተኛ ባለስልጣንን በመግታት በኩል ቁልፍ ሚና አላቸው። የፖለቲካ ድርጅቶች መሰረታዊ አላማቸው መንግስታዊ ስልጣንን ለመጎናፀፍና በሃገሪቱ ሃብት አያያዝ ላይ ያላቸውን የሕዝብ ጥቅም ወይንም የራሳቸውን ድርጅታዊ ጥቅም የሚያራምድ ፖሊሲ ለማስፈጸም ነው።ይኸ ሁኔታ ሁለት ጉዳዮችን ያስነሳል። አንደኛው-- ለህዝብ የቆሙትን ከቀማኞች ለመለየት የጠራ የፖለቲካ ውድድር ስርዓትን መዘርጋት ነው።

> አድልዎ-አልባና የተደላደለ የፓርቲዎች ውድድር መስክ በማመቻቸት እንዲሁም ውዝግቦችን በድርድር በመፍታትና ደንብንና ሕግን በማስከበር አኳያ የሲቪክ ድርጅቶች ትልቅ አስተዋጽዖ

*ሁለተኛው--የተመረጠ ፓርቲ ወደ ሙስናና አምባገነንነት እንዳያዘቀዝቅ ማነቆዎች ሆነው የሚያገግሉ አድልዎ-አልባ ተቋሞችን ማጠንከር ነው።ፖለቲካን ለፖለቲከኞች መተው ቀበሮ በግ ታግድ እንደማለት ስለሆነ የሲቪክ ንቅናቄዎችን መንከባከብ አስፈላጊ ነው።*

**[በ] ሚዛናዊ ቁጥጥር የተዘረጋበት የመንግስት አውታር፦**

*በአገሪቷ ላይ ተዘርግተው የታዩት የመንግስት ስርዓቶች የስራ-አስፈፃሚው አካል በሕግ አውጭና አስፈጻሚ አካላት ላይ ቆራጭ-ፈላጭነቱን አሳይቷል። ስለዚህ ባለስልጣኖችን ገች የሆኑ ተቋሞች ስር ባልሰደዱባት የጮርቃ ዲሞክራሲ ማዕከላዊ ወይንስ ፌደራላዊ፣ ፓርላማዊ ወይንስ ፕሬዝደንታዊ የበትረ መንግስት ስርዓት ይበጃታል የሚለውን ጥያቄ አዲሱ የርዕሰ-ስግ አርቃቂ ሸንጎ በጥሞና እንዲመክርበት ይህ ቻርተር ያሳስባል። በጠቅላላው ተደጋጋሚ ነጻ ምርጫዎችና የፍትህ ሕግ በላይነት ስር እንዲሰድ ከተፈለገ ከሃገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመና ሚዛናዊ የሆነ የመንግስት መዋቅር ረቅቆ ለህዝብ ደምፅ እንዲቀርብ ያስፈልጋል። ፍጹም የህዝብ ታዛዥ መንግስት ስር አስኪሰድም ሕብረ-ሰባው የሆኑ የአርቅና የሽምግልና ባህሎች እንዲቀጥሉ ማድረጉም ኣስፍላጊ ነው።*

## ክፍል ፬ -- የዲሞክራሲ እድገትና የሲቪክ እንቅስቃሴ መንታነት

*የዚህ ቃልኪዳን ይዘት ለሕዝብ ከሚቀርቡ የተለያዩ የፖለቲካ ስርዓቶች ጋር አይጋጭም። ዋነኛው ጥሪ ኢትዮጵያዊያን ካለምንም ተጽዕኖ ከዘመኑ ምኞታቸውና ከክብር ባህላቸው ጋር የሚጣጣመውን የአስተዳደር ስርዓት የመምረጥ መብታቸው ይጠበቅ የሚል ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው የፖለቲካ ፓርቲዎች ተፈጥሮ ባህሪያቸው ስልጣን ለመጎናፀፍ በመሆኑ አድልዎ-አልባና የተደላደለ የውድድር መስክን ለማመቻቸት እንዲሁም በየጊዜው ለሚነሱ ውዝግቦችን በድርድር የመፍታት ባህልን ማጐልመስ በየዘርፉ የተሰለፉ ሲቪክ ድርጅቶች ታሪካዊ ሚናቸው ነው። የፖለቲካና የህግ ተቋሞች ግንባታ ትክክለኛ ፈር እስከያዘ ድረስ የሕዝብ አለኝታ በእነዚህ ተቋዋማት ላይ በአንድ ጊዜ የሚፈጠር ሳይሆን የቀስታ ሂደት እንደሚኖርበትም ማስታወስ ለትግስት ይረዳል።*

*የአሁኑ ትውልድ በዓለም ነፃ ሕዝቦች ማህበረሰብ ውስጥ የሚገባውን ቦታ እንዲያገኝ ለማድረግና የእጣውን ባለቤትነት ለማሳወቅ ቋሚ የነፍስ-ወከፍ እንቅስቃሴ ማድረግ ዋና ቁልፍ ነው። ያልተባበሩ ተሰባበሩ እንደተባለው፣ ምንግዜም የማይታክቱት የኢትዮጵያ ልጆች መብታቸውን ለማስከበር በ‹አገርህን አድን› ርብርብ ላይ ቸል እንደማይሉ እምነታችን ነው። በአዲሱ የኢትዮጵያ ሚሌንየም ወቅት ከሁላችንም የሚጠበቀው ሃላፊነት ከዚህ ያላነሰ ነው። ኢትዮጵያ በልፅጋና በልጆችዋ ተከብራ በነፃነት ለዘለዓለም ትኑር!*

*ግንቦት 17, 2004 ዓ.ም.*
ዋሽንግተን፤ ዲ.ሲ. (አሜሪካ)

ETHIOPIANS HAVE HISTORICALLY ENJOYED STRONG COMMUNAL IDENTITIES THAT ARE UNDER-GIRDED BY UNPRECEDENTED INTERCOMMUNAL TOLERANCE AND MUTUAL RESPECT.

OUR POLITICAL DISCOURSE SHALL HENCEFORTH BE HONEST AND CITIZEN-CENTERED, AND OUR LEADERS SHALL BE JUDGED BY THEIR DEMONSTRATED COMMITMENT TO PUBLIC SERVICE AND ACCOUNTABILITY.

# Citizens Charter for a Democratic Ethiopia

*A Common Cause for Freedom, Prosperity, and National Renaissance*

# የዜጎች ቃልኪዳን ለዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ

***የጋርዮሽ ንቅናቄ ለዴሞክራሲ፣ ለብልጽግናና ለብሄራዊ ተሐድሶ***

**Charter 2012/ቃልኪዳን**